**Amharic/አማርኛ**

**ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ቀጣዩን ዙር የአየር ንብረት ግራንት ፈንድ ይጀምራል**

*በአየር መንገድ ማሕበረሰብ አቅራብያ የአጭር ግዜ ወይ የተለያዩ ዓመታት የአየር ንብረት ፕሮጀክቶች የሚመሰሰሉ እርዳታዎች ይገኛሉ።*

SEATAC – በአየር መንገድ ማሕበረሰብ አቅራያ ያለውን አካባብያዊ አየር ንብረት ለማሻሻል በማሕበረሰብ የሚመሩ ቡድኖች እስከ $20,000 በሲያትል ግራንት ሊያመለክቱ ይችላሉ። የሁለተኛው ዙር የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ የአየር ንብረት ፈንድ ግራንት ፕሮግራም በድምር እስከ $385,000 የሚሰጥ ሲሆን ይህም በቡሪን፣ ደስ ሞኒስ፣ ፌደራል ዌይ፣ ኖርማንዲ ፓር፣ ሲታክና ቱውክዊል ለሚገኘው ማህበረሰብ ያለው የአረንጓዴነት መጠን ለመጨመርና የማሕበረሰብ ለኑሮ አመቺነታቸው ለማሻሻል ነው።

በመጀመርያው ዙር ፈንድ ላይ፣ ወደቡ በተሻለ መልኩ ማሕበረሰቡን ሊደግፍ እንደሚችልና ለዚህ የብዙ ዓመት ፈንድ ለማሕበረሰቡ በማቅረብ እንደሆነ የማህበረሰቡ አመራሮች ምክረ ሀሳብ አቅርበው ነበር። የብዙ ዓመት ፈንድ በወደቡ ላይ የሚኖሩ ማሕበረሰብ ኢንቨስትመንት ተፅኖ እንደሚጨምርና ቀጣይነት ያለው የፕሮጀክት እቅድና አፈፃፀም ለመደገፍ ያግዛል። ወደቡም ይህን ምክረ ሃሳብ በመቀበል አሁን ድርጅቶች ለአንድ፣ ሁለት ወይ ሶስት ዓመት ግራንት በዓመት እስከ $20,000 እንዲያመለክቱ ይጋብዛል።

ኮሚሽነር ፒተር ስቲንብሩክ እንደተናገሩት ‹‹ማህበረሰብ መር ፕሮጀክቶች የካርቦን ልቀት ለመቀነስና፣ በአየር ንብረት ላይ ያላቸውን ተፅኖ ለመቀነስና በዚህ አቅራብያ የሚኖሩትን ማሕበረሰብ ሂወት ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው ቀጣይነት ያለው የወደቡ ስትራተጂ ዋነኛ ክፍል ነው›› ‹‹የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ለረጅም ጊዜ የቆየውን የአየር ንብረት ኢ-ፍትሃዊነት ለመፍታትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማእከል ያደረገ ነው።››

[በሳውዝ ካውንቲ የአየር ንብረት ፈንድ ፕሮጀክት ውስጥ የሚሰሩትን የማህበረሰብ መሪዎችና ወጣቶችን ይተዋወቁ።]()

ለሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ማሕበረሰብ የህዝብ መገልገያ ለማሻሻል፣ የመገልገያ ወይ የስነ ጥበብ ስራዎችን ለመስራት ወይ በአካባቢዎ ፕሮጀክት ለመስራት ወይ የአየር ንብረት እንክብካቤ ፕሮጀክት ለመስራት ፈንድ ቀርቧል። ሀሳብ እቅድ እስከ ጥቅምት 15 2021 ማስገባት አለበት። ግራንቱ ለአንድ ዓመት ፕሮጀክት እስከ $20,000 የሚሰጥ ሲሆን ለብዙ ዓመት ፕሮጀክት እስከ ሶስት ዓመት ለሚካሄድ ፕሮጀክት በየዓመቱ $20,000 ይሰጣል።

ፕሮጀክቱ በህዝብ መገለገያ በታና 3:1 ማሟላት መካሄድ አለበት፤ ማለትም እያንዳንዱ ወደቡ የሚሰጠው ዶላር ግራንት ተቀባዩ ወይ የፕሮጀክት አጋር በሶስት ዶላር መመሳሰል አለበት። ይህን መመሳሰል ለማምጣት ወደቡ የተለያዩ መንገዶችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ የበጎ ፈቃደኝነት ሰዓት፣ ህዝበዊ ሁነቶች ላይ መሳተፍ፣ መገናኛ ሰዓት፣ ለአየር ንብረት አስተዋፅኦ ያደረገና በሂወት ዘመን የተከሉት ተክል መጠን፣ የካርቦን ልቀት መቀነስ፣ በንብረት አስተዋፆ፣ የፕሮጀክት ሂደት አስተዋፆና ጥሬ ገንዘብ ያካትታል።

ሀሳበ እቅዶን እስከ ጥቅምት 15 2021 1:00 ፒኤም ማስገባት ይችላሉ።

ተጨማሪ ዝርዝርና የሀሳበ እቅድ ማተርያሎች በ https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-fund-environmental-grants-program ማግኘት ይችላሉ።

**ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ**

የአየር ንብረት ፕሮግራም ግራንት የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ሲሆን በ2019 በ10$ ሚልዮን የተቋቋመ ነው። የሲያትል ወደብ ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ያቋቋመው ፍታሃዊነት መሰረት ያደረገ አጋርነትና በአየር መንገድ

አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብን ለመደገፍና፣ ድምፅ ብክለት ለመፍታት፣ የአየር ሁኔታ ጤናና ዘላቂነት ድጋፍ የሚሰጥ ነው።

COVID-19 ያደረሰውን በጣም ከባድ ተፅኖ ምክንያት የወደቡ ኮሚሽን ኢኮኖሚያዊ እድገትን እንደ ተጨማሪ የግራንት ፈንድ ጨምሯል።

ማህበረሰቡ COVID-19 ካደረሰው የጤናና ኢኮኖሚ ጫና በሚያገግሙበት ጊዜ፣ ዝቅተኛ የሆነ ፓርክና አረንጓዴ ስፍራ ባለበት በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ኢንቨስት ማድረግ ከሌላው ግዜ በተለየ ያስፈለጋል።

ፕሮግራሙ የፈንዱን ተደራሽነት እድል ለመጨመር ወደቡ ከማህበረሰቡ ጋር የሚሰራበትን መንገድ ላይ ከፍተኛ መንገድ ለውጧል። ከ2020 ጀምሮ ወደቡ ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ቡድኖች፣ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎች እየሰራ ይገኛል፤ ይህም ግራንት ማተርያሎችን በጋራ በመስራትና ግራንቱን ለናስተዋወቅ ዕድል እንዲፈጥርና ማህበረሰቡ ፈንዱን የሚያገኙበትን ዕድል ለመጨመር ማህበረሰብ ተኮር ስልጠናዎች በማዘጋጀት ያሉትን መሰናክሎች ለይቶ ቀርፏል።

ከዚህ በፊት የተሰጡ ግራንቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ዘፌደራል ዌይ ኮርያና አማሪካ ማህበር-- በፌደራል ዌይ የሚገኘውን BPA የኮርያ ጋርደን መገንባትና ለማህበረሰቡ አባላት የባህል ቦታ መገንባት
- በባህል መሃከል ላለው ክፍተት ድልድይ-- ጥቁርና ኢስት አፍሪካ የመጡ ስደተኛ ቤተሰቦችና መደገፍና ወጣቶች ፓርክ እሚያፀዱበት ቀን ማዘጋጀትና የማፅዳት ተነሳሽነት የሚያመጡ በምስራቅ አፍሪካ ቋንቋዎች መፃፍ
- ፑጌት ድምፅ እቀባ ማህበር-- ወጣት መሪዎች ስድተኞችና የስደተኞች ቤተሰቦች ካያክ ፓትሮል በማድረግ እንዲያፀዱ፣ የውሃውን ጥረት መቆጣጠርና ሚሮፕላስቲክ ትምህርት በመስጠት ማጠናከር
- የአየር ሁኔታ ሳይንስ ማእከል-- 1100 ሃይላይን ትምህርት ቤት ዲስትሪክት መዋለ ህፃናት ተማሪዎች በሶስተኛ ደረጃ ሸርቸዋል ቢችና በሲሀርት ፓርክ በቀጥታ ቀረፃና የተቀረፀውን በማሳየት እንዲቆረቆሩ ማድረግ

[ተጨማሪ ስለ Environmental Grant projects> ለማወቅ]